በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ:: አሜን::

*«ሕጻን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነቱም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር ሃያል አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል::»ኢሳ9:6*

አስቀድመን በጌታችንና በመድሃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መንፈሳዊ ሰላምታችንን እናቀርብላችኋለን::

በሰሜን አሜሪካ አህጉረ ስበከት የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ጉባኤ በሰሜን አሜሪካ ውስጥ ለሚገኙ ሰንበት ትምህርት ቤቶች እንኳን ለጌታችንና ለመድሃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል በሰላምና በጤና አደረሳችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ይገልጻል::ነቢዩ ኢሳይያስ አስቀድሞ በትንቢት መነጽርነት ተመልክቶ በተናገረበት የትምህርት ክፍሉ ስለተወለደው ህጻን ሲናገር አለቅነቱ በጫንቃው ላይ የሆነ ታላቅ የሰላም አምላክ እንደሆነ ያስረዳናል:: ነቢዩ በማያያዝም በትንቢቱ የሚወለደው ሕጻን ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆኑን አስረድቷል:: እኛም ደግሞ በሥጋ የተገለጠውን አምላክ በፍጹም ልባችን በፍጹም ሃይላችንና በፍጹም ሕይወታችን ልናገለግለውና ልናመልከው ይገባናል::

ይህንን ታላቅ በዓል ስናከብር ቅድስት ቤተክርስቲያናችን አሁንን ያለችበትን ሁኔታ በትክክል በመረዳት የቤተክርስቲያንን ልጆች የሆንን ሁሉ የሚጠበቅብንን መንፈሳዊ ሃላፊነት በሚገባ በመወጣት መሆን አለበት:: ይህንን ታላቅ ሃላፊነት መወጣት የሚቻለው ደግሞ በተናጥል ሳይሆን በጋራ ሆነን ህብረት ፈጥረን በመተጋገዝና በመተሳሰብ መንፈስ በህብረት ስንሰራ ነው:: ይኸንንም ስራ ለመሥራት ከዛሬ አስር ዓመት በፊት በዚህ በምንኖርበት በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ የሰንበት ትምህርት ቤቶችን አንድነት ለማጠናከርና በጋራ መንፈሳዊ አገልግሎትን ለማከናወን በሰሜን አሜሪካ አህጉረ ስብከት የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ጉባኤ ተመሠረተ::

የአንድነት ጉባኤ በአስረኛው ጠቅላላ ጉባኤ ወቅት የአንድነት ጉባኤውን መተዳደሪያ ደንብ በአዲስ መልክ በማዘጋጀት በሰሜን አሜሪካ በሚገኙ አብያተክርስቲያናት ውስጥ ገብተው አገልግሎት የሚሰጡ ሰንበት ትምህርት ቤቶችን በጋራ በማስተባበር የቤተክርስቲያንን ችግር በጋራ ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ አገልግሎቱን በስፋት ዘርግቷል:: የዲያቢሎስን ሴራ ያፈራርስ ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ ብሎ ቅዱስ ዮሐንስ እንደተናገረው እኛም በጌታችን

መወለድ ፍጹም ሰላምና ፍጹም የአሸናፊነት ሐይል ተቀዳጅተናል:: ስለዚህ በጌታችን መወለድ የዲያቢሎስ ሴራ እንደፈራረሰ ዛሬም በዘመናችን በአለንበት ዓለም በመሐከላችን የመለያየትን ጾር የሚዘራውን ጠላት ዲያቢሎስን በጋራ በመስራት አሸንፈን የቤተክርስቲያንን ትንሳኤ ለማየት እንድንበቃ ሁላችንም በጋራ ሃላፊነታችንን መወጣት እንዳለብን አንድነት ጉባኤው እያሳሰበ በድጋሜ እንኳን ለጌታችንና ለአምላካችን ለመድሃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል በሰላም አደረሳችሁ እያለ በዓሉ የሰላምና የበረከት በዓል እንዲሆንልንላችሁ መልካም ምኞቱን ይገልጻል::

ወስብሀት ለእግዚአብሔር
የአንድነት ጉባኤው ጽ/ቤት

2509 pierce circle Snellville, GA 30078 contact (202) 65-NASSU
Email: eotcnassu@gmail.com// website: www.eotc-nassu.org